# ዜና

## የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

ቅጽ 1 ቁጥር 1 ስልክ ቁጥር 53 01 22 ፖስታ ሣ.ቁ. 700 ኢሜይል eba@telecom.net.et

*ታህሳስ 1996* በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በየሁለት ወሩ የሚታተም


# የፕሬዚዳንቱ መልዕክት

የማኅበራችን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማኅበሩን በሁሉም መልክ ለማጠናከርና የተቋቋመበትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን አቅም ለመገንባት ባለፉት ሦስት ዓመታት ጥረት አድርጓል። በዚህ መሠረት የማኅበሩ አባላት ቁጥር እንዲጨምር ከማድረግ ጀምሮ በማኅበሩ ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ እንዲጠናከርና እንዲጎላ የሚያደርግ ድርጅታዊ ሥራ ተከናውኗል።

የማኅበሩን ጥንካሬ ከሚወስኑት አንዱ የፋይናንስ አቅሙ መሆኑን በመረዳት የማኅበሩ ገቢ የሚጠናከርበትን ስልት በመቀየስ ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል። ማኅበሩ የራሱ ሕንፃ እንዲኖረው ለማድረግ የተጀመረውም ጥረት በአባላቱና በአጋሮቹ ተሳትፎ አበራታች ውጤት እያሳየ ነው።

የማኅበራችንን ዓላማዎች በማስፈፀም ረገድ አባላቱ በተቀናጀ መልክ በነፃ የሕግ አገልግሎት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ፣ አባላቱ ተከታታይ ስልጠና የሚያገኙበትን ዘዴ በማመቻቸትና ተግባራዊ በማድረግ፣ ከፍርድ ቤቶች ኃላፊዎች ጋር በቅርብ በመሥራት፣ የፍትሕ አስተዳደር ሥራ እንዲሻሻል በማድረግ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር በተደራጁ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በመሳተፍ፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ለጅምር ተግባሮቻችን ይበልጥ ጥልቀት ለመስጠት፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግና ሌሎችን አዳዲስ ትልሞችን ለመጀመር የሚያስችል ዓለም አቀፍ ግንኙነት ማጠናከር በማስፈለጉ የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከልዩ ልዩ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት፣ የውጭ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር አስተማማኝ ግንኙነት መሥርቷል። እነዚህን ተግባራት ቀን በቀን በማከናወን ዘላቂነት ያለው ሥራ እንዲሠራ በማሰብም ሁለት የሕግ ባለሙያዎችን በቋሚ ሠራተኝነት ቀጥሯል።

እንደሚታወቀው እስካሁን ማኅበሩ ከአባላቱ ጋር የሚገናኘው በመደበኛ ስብሰባዎች፣ በሴሚናሮችና በወርክሾፖች ነበር። አሁን ማኅበሩ ከአባላቱም ሆነ ከሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ጋር የሚገናኝበት አዲስ መድረክ ጀምሯል። ይህም በየሁለት ወሩ የሚያወጣው **የዜና መጽሔት** ነው።

አሁን ለመነሻ በየሁለት ወሩ የሚወጣው ይህ መጽሔት በማኅበሩ የተከናወኑ ጉዳዮችና መረጃዎች የሚቀርቡበት፣ እንደአስፈላጊነቱ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የማኅበሩ አቋም የሚገለጽበት፣ አጫጭር ትምህርታዊ ርዕሶች የሚወጡበት፣ እንዲሁም ባለሙያዎችን የምናስተዋውቅበት ነው። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር መጽሔት መጀመሩ በራሱ የጥንካሬው አንድ መግለጫ ሲሆን የዚህ ተግባራዊ መገለጫው መጽሔቱ የሚጠበቅበትን በሚገባ ማከናወን መቻሉ ነው። ለዚህ እውን መሆን ደግሞ የሁሉም እገዛ ያሻል።

ስለዚህ ጋዜጣው በመጀመሩ የተሰማኝን ደስታ እየገለጽኩ፣ ለማኅበራችን ጥንካሬ አጋዥና ከፍ ወዳለ መጽሔት የሚያሸጋግረን መሣሪያ እንዲሆን ሁላችንም ለዜና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር መጠናከር የበኩላችንን አስተዋጽኦ እንድናደርግ በማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስም በትህትና አሳስባለሁ።

ጌታቸው ቅጣው
ፕሬዚዳንት

## በአማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች ላይ ወርክሾፕ ተካሄደ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከካናዳ ባር አሶሲዬሽን ጋር በመተባበር በአማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች ላይ የአራት ቀን ወርክሾፕ ከነሐሴ 25 ቀን እስከ ነሐሴ 29 ቀን 1995 በግዮን ሆቴል አካሂዷል። በዚህም ወቅት ብዛታቸው 70 ያህል የሆኑ የሕግ ባለሙያዎች ተካፋይ ሆነዋል። የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ከተሳታፊዎች መካከል ይገኙበታል።

አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሰዎች ችግሮቻቸውን ከፍ/ቤቶች ውጪ የሚፈቱባቸውን ዘዴዎች የሚያመለክት ነው። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ቅጣው በወርክሾፑ መክፈቻ ላይ እንደገለፁት አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች ለጉዳዮች ፍሰት አመራር (Case Flow Management) እና ለፍርድ ቤቶች አሠራር ሥልጠት የሚሰጥ ነው።

ይህ ወርክሾፕ ከካናዳ በመጡ ሦስት ባለሙያዎች ተሰጥቷል። በወርክሾፑ ማጠቃለያም ላይ ለተሳታፊዎች ሰርቲፊኬት ተሰጥቷል።

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተከታታይ የሕግ ትምህርት ፕሮግራም ጀመረ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የተከታታይ የሕግ ትምህርት ፕሮግራም ጀምሯል። ይህንኑም ፕሮግራም በዳይሬክተርነት እንዲመሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዳኛ የነበሩትን አቶ ሣሙኤል ኃይለጊዮርጊስን ቀጥሯል። ይህም ፕሮግራም በካናዳ ባር አሶሲየሽን የገንዘብ ድጋፍ የሚንቀሳቀስ ነው።

የፕሮግራሙ ዓላማ በሥራ ላይ ላሉ የሕግ ባለሙያዎች የሥራ ላይ ሥልጠናዎችን መሥጠትና ልዩ ልዩ መጽሔቶችን ማዘጋጀት ይሆናል።

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በመላው አፍሪካ ጠበቆች ማኅበር ሁለተኛ ካውንስል ስብሰባ ላይ ተካፈለ

የመላው አፍሪካ ጠበቆች ማኅበር ሁለተኛ ካውንስል ስብሰባ ጥቅምት 7 ቀን 1996 ዓ.ም. ካርቱም ሱዳን ውስጥ ተካሄደ። የመላው አፍሪካ ጠበቆች ማኅበር መሥራች የሆነው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በዚሁ ስብሰባ ላይ ተካፍሏል። አቶ ወልደሥላሴ ብርቱ፣ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ም/ፕሬዚዳንት እንደገለፁት ስብሰባው በብዙ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎች ማሳለፉንና የተሳካ እንደነበር ገልፀዋል። በተጨማሪም የሱዳንን ጠቅላላ ፍ/ቤት፣ ፍትሕ ሚኒስቴርንና ፓርላማ የመጎብኘት ዕድል እንዳጋጠማቸው ገልፀዋል።

በአሁኑ ወቅት የማኅበራችን ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ጌታቸው ቅጣው የመላው አፍሪካ ጠበቆች ማኅበር ዋና ፀሐፊ በመሆን እያገለገሉ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

## የነፃ የሕግ አገልግሎት ሰጪዎች ሴሚናር በኢንተቤ ኡጋንዳ ተካሄደ

የነፃ የሕግ አገልግሎት ሰጪዎች ሴሚናር ከሰኔ 2-6/1995 ዓ.ም. በኢንተቤ ኡጋንዳ ተካሄደ። ይህንን ሴሚናር በኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም የሚመራ 5 ተሳታፊዎች የሚገኙበት ልዑክ ተካፍሏል። ሴሚናሩ የተዘጋጀው በኡጋንዳና በእንግሊዝና ዌልስ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት ትብብር ነበር።

## የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት በሼራተን አዲስ ተካሄደ

"የሕግ ባለሙያዎች ምሽት" ቅዳሜ ሐምሌ 26 ቀን 1996 ዓ.ም. በሼራተን አዲስ ተካሄደ። ከምሽቱ መግቢያ ቲኬቶች ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ የማኅበሩን ዋና መሥሪያ ቤት ለማሰራት ይውላል።

በዚህም የምሽት ፕሮግራም ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ዳኞችንና ጠበቆችን ጨምሮ ከ700 በላይ ሰዎች ተሳትፈዋል።

## የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የዓለም አቀፍ ባር አሶስዬሽን ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ተካፈለ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በፕሬዚዳንቱ በአቶ ጌታቸው ቅጣው በመወከል መስከረም 17 ቀን 1996 ዓ.ም. በሳንፍራንሲስኮ አሜሪካ በተካሄደው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ተካፍሏል።

## የተከታታይ የሕግ ትምህርት ወርክሾፕ በናይሮቢ ኬንያ ተካሄደ

በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል በአቶ ዓለሙ ደነቀው የተመራ ሦስት አባላት ያሉት ልዑክ በናይሮቢ ኬንያ፣ ከሕዳር 2-4/1996 ዓ.ም. የተካሄደውን ወርክሾፕ ተካፍሏል።

ወርክሾፑ የተከታታይ የሕግ ትምህርት ሰጪዎችን ብቃት ለማሳደግ የታቀደ ነበር። ይህ ወርክሾፕ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በቅርቡ ለጀመረው የተከታታይ የሕግ ትምህርት ፕሮግራም ይጠቅማል ተብሎ ይታመናል።

ወርክሾፑ በካናዳ ባር አሶሲዬሽን ድጋፍ የተዘጋጀ ነበር።